724/2013

H1-85200250/7
9/1/2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development and Construction

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ

ክ/ል/ኮ/ሚ

ጉዳዩ፣ የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ

የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት የፓናል ውይይት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 28/2005 ሆኖ ከጳጉሜ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀደቀ መሆኑ ይታወቃል።

በዚሁ መሰረት መመሪያውን እንድታስፈጽሙ የፀደቀው መመሪያ 1 ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን እየገለጽን የሰነዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም እንድትከታተሉት እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

ግልባጭ፣

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ከተማ ልማት ዘርፍ/
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ኮንስትራክሽን ዘርፍ/
- ለሀብት ሥራ አመራርና ማስተባበሪያ ቢሮ
- ለህግ አገልግሎት መምሪያ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት አብይ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት ቴክኒክ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት የፓናል ውይይት ዝግጅት ኮሚቴ

ክ/ል/ኮ/ሚ

5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት

የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት

ETHIOPIAN CITIES WEEK

# የፓናል ውይይት የአፈጻጸም መመሪያ
# ቁጥር 28/2005

ጳጉሜ /2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች ዕድገትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና ትብብር በማጠናከር፣ መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት፣ እንዲሁም የከተሞችን እሴቶች በማስተዋወቅና በማጎልበት ጠንካራ መሰረት ያለዉ የከተማ ህዝብ ንቅናቄና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ዓመታዊ የከተሞች ሳምንት ተሰይሟል፡፡ በዚህም መሰረት 5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን "ከተሞቻችን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማዕከላት በመሆን የመለስን ሌጋሲ ያስቀጥላሉ" በሚል መሪ ቃል በባህርዳር ከተማ ከህዳር 11 -17 ቀን 2006 ዓ.ም. ይከበራል፡፡

የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በዓል ዓላማን ለማሳካት ከሚከናወኑት ዋና ዋና ተግባራት መካከል የሴሚናርና የፓናል ውይይት ዝግጅት አንዱ ነው፡፡ በዚህ ዝግጅት በከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተቀረጹ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች አፈጻጸምና ተግዳሮቶች እንዲሁም የተቀመሩ ልምዶችና ተሞክሮዎች ዙሪያ ያተኮሩ ጽሁፎች በዋነኝነት የሚቀርቡ ሆኖ ከዚህ በተጨማሪ ከዘርፉ ስራዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ የጥናት ጽሁፎችም የሚቀርቡና ውይይት የሚደረግባቸው ይሆናል፡፡

እነዚህ የፓናል ውይይቶች የከተማ ልማት የትኩረት መስክ በሆኑት የከተማ ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ዙሪያ በከተማ ልማት ባለድርሻ አካላት ዘንድ የጋራ መግባባትን እና ትክክለኛ ግንዛቤን ለመፍጠር ከሚኖራቸው ከፍተኛ ፋይዳ አንጻርም በርካታ አካላት ተሳታፊ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ በዚሁ መሠረት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከፍተኛ የአመራሮች፣ የቢሮ ዋና ዳይሩክተሮች የመምሪያ ዳይሬክተሮች፣ የክልል የከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊዎችና ምክትል ኃላፊዎች፣ ስራ ሂደት ባለቤቶች፣ የአዲስ አበባና የድሬደዋ የከተሞች የኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮ ኃላፊዎች፣ የከተማ ከንቲባዎችና ስራ አስኪያጆች፣ የክልል ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ ኃላፊዎች፣ የክልል ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ቢሮ (ኤጀንሲ) ኃላፊዎች ፣ የክልል ቴክኒክና ሙያ የብቃት ማረጋገጫ ማዕከል ዳይሬክተሮች፣ ተጋባዥ ኮንትራክተሮች፣ አማካሪዎች፣ የክልልና ከተሞች የአነስተኛ ብድር አቅራቢ ተቋማት፣ በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር የተመረጡ የባህር ዳር ከተማ ነዋሪዎች፣ ተጋባዥ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተወካዮች፣ በከተማ ልማት ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት፣ በከተማ ልማት ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በዚህ ውይይት ላይ የሚገኙ ይሆናል፡፡ የፕሮግራሙ አላማ፣ የሚጠበቅ ውጤት፣ ውይይት የሚደረግባቸው ርዕሰ ጉዳዮች፣ ቦታ፣ ቀንና በጀትን በተመለከተ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የ5ኛው የከተሞች ሳምንት የፓናል ውይይት ዝግጅት መመሪያ ቁጥር 28/2005 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በ5ኛው ዙር የከተሞች ሳምንት የፓናል ውይይት በሚሳተፉ አካላት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

### 3. የፓናል ውይይቱ ዓላማ

የሴሚናርና የፓናል ውይይቶች ዝግጅት ዋና ዓላማ በከተማ ልማትና በኮንስትራክሽን ዘርፍ የትኩረት መስክ በሆኑት አበይት ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በተለያዩ የከተማ ልማት ባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር፣ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲፈጠርና የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ ነው።

### 4. ከፓናል ውይይቶች የሚጠበቁ ውጤቶች

1) በተመረጡ የትኩረት መስኮች ዙሪያ በሚቀርቡት ጽሁፎችና በሚደረጉት ውይይቶች መንግስት ያወጣቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ትግበራ ተጠናክረውና ተፋጥነው የሚፈጸሙበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥ[illegible]

724/2013

2) በከተሞች፣ በከተማ ልማት ባለድ[illegible] ነዋሪው መካከል የመረጃ፣ የእውቀት እና የልምድ ልውውጥ ይካሄዳል።
3) በተመረጡት ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ መግባባትና ግንዛቤ ይፈጠራል።
4) በዝግጅት ላይ ለሚገኙ ረቂቅ ሰነዶች ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶች እንደሚገኙ ይጠበቃል።

### 5. የፓናል ውይይቶች የሚካሄድባቸው ጊዜያት፣

በ5ኛዉ የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት የሚዘጋጁት ሴሚናርና የፓናል ውይይቶች ከህዳር 12 -16/ 2006 ዓ.ም በየቀኑ ከሰዓት በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ይከናወናሉ።

The Federal ... Republic of Ethiopia ... of Urban Development & Construction

6. ሰነዶችን ሊያቀርቡ የሚችሉ አካላትና የሚያቀርቧቸው ርዕሰ ጉዳዮች

ለውይይት የሚቀርቡት ርዕሰ ጉዳዮች በሚከተሉት ሦስት ክፍሎች የሚካተቱ ይሆናሉ፡-

1) በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሴክተር በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የተካተቱ ዋና ዋና ተግባራት /Pillars/ መሰረት በማድረግ የተቀረጹ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ይዘትና የትግበራ ሂደት ላይ ያጠነጠኑ ጽሁፎች ሲሆኑ እነዚህም፡-

   ሀ/ የስራ እድል ፈጠራን በተመለከተ (በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትየማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ስኬችና ተግዳሮች የሚል እና The Role of Micro and Small Enterprises fo sustainable Economic Development and Structural Transformation: The Ethiopian Experience)

   ለ/ የመኖሪያ ቤት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች አተገባበርና አፈጻጸም፣ ስኬቶቹና ፈተናዎቹ በሚል የአዲስ አበባ ከተማ ተሞክሮ በጥናት ላይ ተመስርቶ የሚዘጋጅ ጽሁፍ፣

   ሐ/ በመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ከሊዝ አዋጅ አፈጻጸም አንጻር ስኬቶቹንና ተግዳራቶቹን አስመልክቶ በጥናት ላይ የተመሰረተ ጽሁፍ፣

   መ/ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣

   ሠ/ በከተሞች ፕላን ጽዳትና ዉበት ዙሪያ ( የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ"የአረንጓዴነት ልማትና ውበት)

   ረ/ የልማታዊ ኮሚኒኬሽን ስትራቴጅ፤ ሲሆኑ፣

2) ከሀገር ውስጥ እና ከውጪ ሀገራት የተገኙ ተሞክሮዎች ላይ ተመስርተው የተዘጋጁ ጽሁፎች ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል፡-

   ሀ/ የትግራይ ከተሞች በከተማ ፕላን አፈጻጸም፤ በጽዳትና የእናቶች አደረጃጀትና መልካም አፈጻጸም ተሞክሮዎች ፡፡

   ለ/ የደብረ ማርቆስ ከተማ የከተሞች የመበደር ስልጣን መልካም አፈጻጸም ተሞክሮ፣

3) በተለያዩ አካላት የተዘጋጁ ጥናታዊ ጽሁፎች

ሀ/ Ministry of Urban De 724/2013 t and Construction Annual Statistical Abstract Analytical Report (2000 — 2004 E.C)

ለ/ የባህርዳር ከተማ ከምስረታ እስከ 2006 ዓ ም በሚል የጥናት ጹሁፍ እና

ሐ/ የአረንጓዴነት ልማትን ከተሞች ውበት በዲላ የደን ኮሌጅ የተዘጋጀ ጥናታዊ ጽሁፍ

መ/ ሌሎች ለቴክኒክ ኮሚቴው ቀርበው ተቀባይነት የሚያገኙ ጽሁፎች የሚቀርቡ ይሆናል፡፡

ሰነዶችን የሚያዘጋጁ አካላትና የርዕስ ጉዳዮች ምርጫ ለቴክኒክ ኮሚቴ ቀርቦ በሚወሰነው መሰረት ይሆናል፡፡

## 7. በፓናሉ የሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዮች ይዘት

በፓናሉ የሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዮች ከላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ጉዳዮች መሰረት ተደርጎ የሚዘጋጅ ሲሆን ይዘታቸውም በሚከተለው መንገድ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

1) መግቢያ
2) አላማ
3) ስለ ጉዳዩ ያሉ ጽንሰ-ሀሳቦች ወይም እውነታዎች (Realities)
4) በጉዳዩ ላይ ያለው የመንግስት አቅጣጫ (government policies and strategies)
5) እስከ አሁን የተገኙ ውጤቶች (success stories and practices)
6) ችግሮች ወይም ተግዳሮቶች (challenges) እንዲሁም
7) ጠቋሚ መፍትሄ (solutions or tools) ወይም ባለድርሻ አካላት ማድረግ ስላለባቸው ጉዳዮች
8) ማጠቃለያ እንዲኖረው ተደርጎ ሰነዶች ይዘጋጃሉ፡፡

## 8. የፓናል ሰነዶችን ለመምረጥ የምንጠቀምበት መስፈርት

1) በ5ኛው የከተሞች በዓል አከባበር መሪ እቅዱ ከተዘረዘሩት 7ቱ የከተማ ልማት ዘርፍ ፒላርስ ከአንድና ከዚህ በላይ ስራዎች ጋር ተዛማጅነት ያላቸው፣

2) በተለያዩ ከተሞች በተግባር የተፈተሸ ወይም ተሞክሮዎችን ያካተተ፣
3) በቀጣይ ከተማ ስራዎችን ላይ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል፣
4) ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው፣
5) የሀገራችንን ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን የሚያከብር፣ የከተማ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን የሚያስፈጽም፣
6) ግልጽና በከተሞቻችን አብይ ችግሮች ማለትም በልማትና በመልካም አስተዳደር ችግሮች አፈታት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ፣
7) ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች መሰረት መሆናቸው ተጣርቶ በሚመለከተው የሚኒስቴር መስሪያቤቱ ቢሮ ይሁንታ አግኝቶ ያለፈ
8) በአብይና በቴክኒክ ኮሚቴው ተቀባይነት ያለው ናቸው።

## 9. ጥናታዊ ጽሑፉ አቀራረብ፣የሚሰጠው ጊዜና ሁኔታ

ጥናታዊ ጽሑፉ በየሚመለከታቸው ቢሮዎች በኩል እስከ መስከረም 25/2006 በየሚመለከታቸው ቢሮዎች በኩል ተዘጋጅቶ ለፓናል ዝግጅት ለአስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ይላካል።

ጥናቱ በMS-Word እና በMS-Power point ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ሲሆን፣ የጽሁፍ ይዘትም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ያወጣው የውይይት ሰነድ ፓወር ፖይንት አቀራረብ ስታንዳርድ




[redacted]

?? ?? ???--

???? ? ?? ??...

ሆኖ

1) በMS-Word የሚዘጋጀው ጽሑፍ font 11 ሆኖ space 1.5 ብዛቱ ከ15 ገጽ ያልበለጠ እንዲሆን
2) በMS-Power point የሚዘጋጀው ከ12 slides ያልበለጠ እንዲሆንና font ርዕስ 32፣ ውስጥ ጽሁፍ 28
3) ጽሑፎቹ በአማርኛ የሚዘጋጁ ሆነው ፎንታቸው ቢቻል Power Geez Unicode 1 ቢሆን
4) ጽሑፎቹ በHard እና Soft ኮፒዎች ተዘጋጅተው ይላካሉ

10. ክፍያዎችን በተመለከተ፡-

1) ለጥናታዊ ጽሁፍ አቅራቢዎች የሚፈጸም ክፍያን በተመለከተ፣

በ5ኛው የከተሞች ሳምንት በሚዘጋጀው የፓናል ውይይት መድረክ ላይ ጥናታዊ ጽሁፍ ላዘጋጁና ለሚያቀርቡ ባለሙያዎች በአንድ የጥናት ጽሁፍ ብር 5000.00 ( አምስት ሺህ ብር) የሚከፈል ይሆናል፡፡

2) የአበል ክፍያን በተመለከተ፣

ሀ) በ5ኛው የከተሞች ሳምንት በሚዘጋጀው የፓናል ውይይት መድረክ ላይ ለመሣተፍ ከባህርዳር ከተማ አስተዳደር ከ 21 ቀበሌዎች ከሴት፣ ከወጣትና ከነዋሪ የተመረጡ የባህርዳርና አካባቢው ከተማ ነዋሪዎች ተሳታፊዎች ሙሉ ሥማቸው ከተወከሉበት ቀበሌ አግባብነት ባለው አመራር በድብዳቤ በሚላከው ዝርዝር መሠረት የፓናል ውይይት

ለሚካሄድባቸው 5 (አምስት) ቀናት ብቻ በቀን 50 ብር የትራንስፖርት አበል ይከፈላቸዋል።

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) የተመለከተው ክፍያ የሚፈጸመው ሁሉንም የፓናል ውይይት መድረኮች መሳተፋቸው በሠዓት መቆጣጠሪያ ፎርማ ለተረጋገጠላቸው ተሳታፊዎች ብቻ ነው።

## 11.የፓናል ውይይት የሚካሄድባቸው ቀናት

የከተሞች ሳምንት በዓል ዝግጅት ኮሚቴ የፓናል ውይይት የሚካሄድበት ቦታና ፕሮግራም ለጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢዎችና ተሣታፊዎች ከበዓሉ ዝግጅት ቀደም ብሎ ያስታውቃል። በዚህ የሴሚናርና የፓናል ዝግጅት ላይ 12 ጥናታዊ ጽሁፎች በ12 አቅራቢዎች ይቀርባል። በዋናነት በየቀኑ ጠዋት ጠዋት ሁለት ሁለት ሰነድ እንደሚቀርብ ታሳቢ በማድረግ በአጠቃላይ ለፓናል ውይይቱ 5 ቀናቶች ያስፈልጋል። ውይይቱም መክፈቻና መዝጊያ ቀናቶችን ሳያካትት ከህዳር 12-16 2006 ዓ፣ም ባሉት አምስት ቀናት ይቀርባል።

## 12. የፓናል ውይይቶች የሚካሄድበት ቦታ

የፓናል ውይይቱ በባህርዳር ከተማ በተመረጠ አንድ የስብሰባ አዳራሽ ይካሄዳል። የስብሰባ ቦታውም ከባህርዳር ከተማ አስተዳደር ጋር በመተባበር ይዘጋጃል፡ ፡ እስከ 750 ሰው ሊይዝ የሚችል ደረጃውን የጠበቀ  የስብሰባ አዳራሽ ኢግዚቢሽኑ ከሚካሄድበት አካባቢ እንዳይርቅ በማድረግ እንዲዘጋጅ የሚደረግ ሲሆን ለትራንስፖርት አመቺ የሆነና የድምጽ ብክለት የሌለበት የስብሰባ አዳራሽ እንዲሆን ይደረጋል። በፓናል ውይይቱ ሁሉም የከተሞች ሳምንት ተሳታፊ ከተሞችና ክልሎች ተወካዮቻቸው በአዳራሹ እንዲገኙ ይደረጋል።

## 13. የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

1) የፓናል ንዑስ ኮሚቴው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚገኙ ቢሮዎችንና ተጠሪ ተቋማትን በማግኘት በተጠቀሱት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሰነድ ሊያቀርቡ የሚችሉባቸውን ርዕሶችና አካላትን መነሻ ይወስዳል፣

2) ሰነድ ሊያቀርቡ የሚችሉ ተቋማትን እና ርዕሰ ጉዳዮችን እንዲሁም በሰነዶቹ ይዘት ላይ ሉቴክኒክ ኮሚቴውና ለአብይ ኮሚቴው በማቅረብ ያስወስናል፣

3) ከተመረጡ ተቋማት እና ግለሰቦች ጋር በደብዳቤ፣ በአካልና በስልክ በመገናኘት ሰነዶቹ ተጠናቀው ከጊዜ ገደቡ በፊት እንዲገቡ ይደረጋል።

4) የተዘጋጁ ጽሁፎች በተያዘላቸው/በተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ መቅረብ የሚችሉ መሆኑን ለማየት በተቻለ አቅም ከማቅረቢያ ቀን በፊት እንዲቀርብ ተደርጎ ይገመገማል።

## 14.መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ ከጳጉሜ 01 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

## 15.መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል።

**መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማሪያም**

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር**

አባሪ 1. የሴሚናርና የፓናል ውይይቶች ተሳታፊዎች (750 ሰዎች ይሳተፋል)

| ተ.ቁ | የተሳታፊዎች አይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | የውይይት ሰነድ የሚያቀርቡ 12 የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች | 13 |
| 2 | የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራር 3 አባላት፣ 1 አማካሪ 13 የቢሮና የተጠሪ ተቋማት ኃላፊዎች፣ 50 መምሪያ ኃላፊዎች፣ በኢግዚቢሽኑ ከሚሳተፉ ቢሮዎች የመጡ 10 ባለሙያዎች | 77 |
| 3 | የ9 ክልልና የ2 ከተማ አስተዳደር የከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊዎች፣ ምክትልና ፣ስራ ሂደት ባለቤቶች፣ አንድ ባለሙያ | 44 |
| 4 | ከ150 ተሳታፊ ከተሞች የሚመጡ የከተማ ስራ አስኪያጅና ከንቲባዎች | 300 |
| 5 | 11 የክልል ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ ኃላፊዎች፣ 11 ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ቢሮ (ኤጀንሲ) ኃላፊዎች ፣ 11 የክልል ቴክኒክና ሙያ የብቃት ማረጋገጫ ማዕከል ዳይሬክተሮች፣ ኤጀንሲ 2 ኮንትራክተሮች፣ 2 አማካሪዎች፣ 4 የአነስተኛ ብድር አቅራቢ ተቋማት | 41 |
| 6 | በባህርዳር ከተማ አስተዳደር በ21 ቀበሌዎች ከሴት፣ ከወጣትና ከነዋሪ የተመረጡ የባህርዳርና አካባቢው ከተማ ነዋሪዎች በየቀበሌው አስር ሰው | 210 |
| 7 | ከባህርዳር አካባቢ ከተሞች ከዳንግላና 10 ከወረታ 10 (ለኢግዚቢሽኑ ከመጡ ሰዎች ውስጥ) | 20 |
| 8 | በከተማ ልማት ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰሩ ሲቪል ማህበራትና ተባባሪ አካላት | 40 |
| 9 | የንዑስ ኮሚቴ አበላት | 5 |
| | ድምር | 750 |